የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13 እና 14

1. ጌታችን ያበረከተው አምስት እንጀራ እና ሁለት ዓሳ ስንት መሶብ ተረፈው?
ሀ)9 ለ)11 ሐ)12 መ)15

2. በአባቶቻችን አስተምህሮ መሰረት ህፃናት ያልተቆጠሩበት ምክንያት ምንድን ነው?
ሀ) ከሚበሉት የሚፈረፍሩት ስለሚበልጥ
ለ) ህፃናት ጭራሹንም ስለማይበሉ
ሐ) ጓዳ ነው እንጂ በሰው ፊት ብዙ ስለማይበሉ
መ) ሁሉም

3. ጌታችን ለስንት ሰዎች አምስት እንጀራ እና ሁለት ዓሳ መገበ?
ሀ)ሴቶች እና ህፃናት ሳይጨመሩ አምስት ሺህ
ለ) ሴቶች እና ህፃናት ጨምሮ አምስት ሺህ
ሐ) አምስት ሺህ ሴቶችን እና ሕፃናት
መ) መልስ አልተሰጠም

4. በውሀ ላይ እንዲራመድ ጥያቄ የጠየቀው ሐዋርያ ማን ነው?
ሀ) ጴጥሮስ ለ)ዮሐንስ ሐ) ያዕቆብ መ)ይሁዳ

5. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በምሳሌ አስተማረ?
ሀ) በትንቢት አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ ስለተባለ
ለ) ሕዝቡ በምሳሌ ሲያስተምራቸው በይበልጥ እንዲገባቸው
ሐ) ያለ ምሳሌ ማስተማር ስለማይችል
መ)ሀ እና ለ

6. የስንዴው እና የእንክርዳዱ እጣ ፋንታ ምን ሆነ?
ሀ)ሁለቱም ወደ ጎተራ ተከተቱ
ለ) ስንዴውን ወደ እሳት እንክርዳዱን ወደ ጎተራ አስገቡት
ሐ) ስንዴውን ወደ ጎተራ እንክርዳዱን ወደ እሳት አስገቡት
መ) ሁለቱንም ወደ እሳት ጨመርዋቸው

7. ዘር እና ዘሪ ተብለው የተመሰሉት ምንድን እና ማን ናቸው?
ሀ) ቁርባን እና ሐዋርያት
ለ) ወንጌል እና ጌታችን
ሐ) ዕጣን እና መላእክት
መ) ብሉይ ኪዳን እና ሐዋርያት

8. በጭንጫ ላይ የወደቀው ዘር ትርጉም ምንድን ነው?
ሀ) በመጀመርያ ቃሉን በደስታ የሚቀበለው ነገር ግን በቃሉ ምክንያት መከራ ሲመጣ መቋቋም ሚያቅተው
ለ) ክፉ ዲያቢሎስ የተማረውን ቃል ሳያድግ የሚወስድበት
ሐ) ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል
መ) መልስ አልተሰጠም

9. በመንገድ ዳር የተዘራው ዘር ምሳሌ ላይ ወፎች ተብለው የተጠቀሱት ምንድን ናቸው?
ሀ) ቅዱሳን መላእክት ለ) ክፉ(አጋንንት) ሐ)ርግቦች መ)ሁሉም

10.ዘሪ ዘሩን ከዘራባቸው ቦታዎች ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) መንገድ ላይ ለ)ጭንጫ ላይ ሐ)ወፎች ጎጆ ውስጥ መ)እሾህ መካከል

11. በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ላይ ታንኳው ሲናወጥ ጌታ ወዴት ነበር?
ሀ) ተኝቶ ለ) ሕዝቡን ሊያሰናብት
ሐ) ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጥቶ መ) ለ እና ሐ ሠ) ሁሉም
12."መንግሥተ ሰማያት ሴት ወስዳ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የለወሰችውን፣ ሁሉንም እንዲቦካ ያደረገውን እርሾ ትመስላለች።" ማለት?
ሀ) ወንጌል ለ 3ቱም ነገድ(ለሴም፣ ለያፌት እና ለካም) መሰጠቷን
ለ) ጌታ ሦስት ሌሊት ሦስት መዐልት በከርሠ መቃብር ቆይቶ ሙስና መቃብርን አጥፍቶ በ አንድ ወገን ሁኖ መነሳቱን
ሐ) መንፈሳዊ ሥራ በወጣኒነት፣ በማዕከላዊነት እና በፍጹምነት ተሰርቶ በዛው ልክ ክብርን እንደሚያወርስ
መ) ቀሳውስት ሥጋ ወደሙን "ለቀድሶተ ሥጋ ወነፍስ ወመንፈስ" ብለው ይሰጣሉና በሥጋ ወደሙ ሁሉ መከበሩን ለማሳየት
ሠ) ሁሉም

13.በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ላይ 30 ፍሬ ያፈራሉ የተባሉት በአጠቃላይ ለማን ነው?
ሀ) ለሰማዕታት
ለ) በሕግ የጸኑ የዓለም ሰዎች
ሐ) ነገስታት
መ) መነኮሳት

14.የሰናፍጭ እና የሕገ ወንጌል መመሳሰል ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
ሀ) ሰናፍጭ ቁስለ ስጋን እንደምታደርቅ ወንጌልም ቁስለ ነፍስን ታደርቃለች
ለ) ሰናፍጭ ፍጽምት ናት ነቅ የለባትም ፤ ወንጌልም ነቅዓ ኑፋቄ የለባትም
ሐ) ሰናፍጭ ጣዕሚ ምረሯን ያዘነጋዋል፤ ወንጌልም ተስፋዋ መከራዋን ያዘነጋዋል
መ) መልሱ የለም

15."እንክርዳዱን ስታርሙ ስንዴውንም ጨምራችሁ እንዳትነቅሉ አይሆንም" የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው?
ሀ) ኃጥአንን ከጻድቃን መለየት ለመላዕክት የማይቻል ስለሆነ
ለ) ከኃጥአን ተወልደው በንስሐ የሚመለሱ ይኖራሉና
ሐ) ጌታ ከኃጥአን ይልቅ ለጻድቃን ስለተጨነቀ
መ) ሁሉም

16.ከሚከተሉት ውስጥ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ካሉት ምሳሌዎች ውስጥ አይካተትም።
ሀ) የስንዴ እና የእንክርዳድ ምሳሌ
ለ) የሰናፍጭ ቅንጣት ምሳሌ
ሐ) የወይኑ ባለቤት ምሳሌ
መ) ስለ እርሾ ምሳሌ

17.በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ላይ 60 ፍሬ ያፈራሉ የተባሉት በአጠቃላይ ለማን ነው?
ሀ) ለሰማዕታት
ለ) በሕግ የጸኑ የዓለም ሰዎች
ሐ) ነገስታት
መ) መነኮሳት

18."መስማትን ትሰማላችሁ፤ አታስተውሉምም፤ ማየትንም ታያላችሁ፤ አትመለከቱምም...በዐይናቸው እንዳያዩ፤ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፤ በልባቸውም እንዳያስተውሉ ተመልሰውም እንዳልፈውሳቸው ልባቸውን አደንድነዋልና..." የሚለውን ትንቢት የተናገረው የትኛው ነቢይ ነው?
ሀ) ነቢዩ ኤርምያስ
ለ) ነቢዩ ኢሳይያስ
ሐ) ነቢዩ ሆሴዕ
መ) ነቢዩ ዘካርያስ

19."ላለው ይሰጡታል፤ ይጨምሩለታልም፤ የሌለውን ግን ያንኑ ያለውን ቅሉ ይወስዱበታል። " የሚለው ምን ማለት ነው?
ሀ) ለሀብታም ሰው ብር ይጨምሩለታል፤ ከድሀው ግን ይወስዱበታል
ለ) የሚያስተውል አእምሮ ላለው ምሳሌውን ይነግሩታል
ሐ) ጤና ለጎደለው ሕመም ይጨምሩለታል
መ) ሁሉም

20. በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ላይ 100 ፍሬ ያፈራሉ የተባሉት በአጠቃላይ ለማን ነው?
ሀ) ለሰማዕታት
ለ) በሕግ የጸኑ የዓለም ሰዎች
ሐ) ነገስታት
መ) መነኮሳት